Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Higher level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau supérieur – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel superior – Prueba 1

Wednesday 4 May 2016 (afternoon)
Mercredi 4 mai 2016 (après-midi)
Miércoles 4 de mayo de 2016 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a literary commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire littéraire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[20 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario literario sobre un solo pasaje.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.



2216 – 0009
© International Baccalaureate Organization 2016

International Baccalaureate
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

https://xtremepape.rs/

ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ ስነጽሁፋዊ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።

**1.**

አሰለቸሁህ እንዴ? ምን ላድርግ ብለህ ነው… የዚህ ሠፈር ሰዎች ከሞት ጋር ጨዋታ እያሉ… ሞትን እኔ የፈጠርኩት ይመስል… ስሜን እንኳን የሚጠሩት ከመካከላቸው ሞት አንዱን ሲጎበኘው ብቻ ነው። በዚያ ላይ ዝምታህን ወድጄዋለሁ።

ታውቃለህ? ሞት ለእኔ የገቢ ምንጭ ነው… እንጂማ እኔ ራሴ ሞት… በስመአብ በል! ይኼን እጄን ታየዋለህ? ሰላሳ ዓመት በላይ ከዶማና አካፋ በቀር የጨበጠው የሰው ልጅ ዛሬ የአንተን ብቻ ነው… ሞት ነጠቀብኝ እንጂ አንዳንዴ ጃምቦ ይጨብጠኝ ነበር… ጃምቦ የዕድሩ ጡሩምባ ነፊ። መሸት ሲል ከየሺ ቤት ወደዚህ መጥቶ ነበር የሚያሳርገው። እኔን ጨብጦ የሞተ የመሰላቸው ታድያ ለሞላ ነግረውት ይኸው የእሱ ሰላምታ ጭንቅላቱን በመወዝወዝ ብቻ ሆኗል።

አሁን በቀደም የየሺ ሶስተኛ ልጅ ሞተና ሞላ በማለዳ ከቤቴ መጥቶ በስንት መከራ ጠጋግኜ ያቆምኳትን የሳንቃ በሬን በዚያ ሰፊድ እጁ ሲደበድባት መቀርቀሪያዋን ገንጥሎ ጣለብኝ። “ምነው ሞላ!  በሬን ከምታወልቅ ቀስ ብለህም ብትጠራኝ እኮ እሰማህ ነበር” አልኩት… በትህትና። እሱ እቴ! ከመጤፍም አልቆጠረኝ… “ጋሽ በትረ… የየሺ ልጅ ሞታለች፣ መቃብር ሄደው ያዘጋጁ” አለኝና ከባድ ሥራ እንዳለበት ሰው ጡሩምባውን እያስተካከለ በዚህ ሽቅብ ወጣ።

አሁን የየሺ ልጅ ሞት ምን አዲስ ነገር ሆኖ ነው… ወርቄን ከሰፈሩ ወንድ ያላስወለደ እኔ ብቻ ሳልሆን እቀራለሁ… ያንን ሁሉ መዓቲ ፈልፍላ ምን እንደምታበላቸው ሳስብ ይደንቀኛል። …እንደው ልጄ በቀደም የባሻ ቀብር ላይ ነው በዘመኔ ፍታት ሲደረግ ያየሁ… ሌላውንማ ማን ሰው ብሎት ፍታት ያደርግለታል… በቆፈርኩት ጉድጓድ ይጣልና ድንጋይ ይነባበርበታል… ታድያ መምሩ የዚያን ቀን “ጥንት ፈጣሪ መና ከሰማይ ያወርድ ነበር” እያሉ ሲናገሩ የሰማሁት እውነት ይሆን? ብዬ ከነከነኝ። መቼም ለየሺ ዛሬም በምስጢር እንዲያ እያደረገላት ካልሆነ የእሷ ካቲካላ ተሸጦ አሁን ለዚያ ሁሉ መዓቲ ዳቦ ሊሆን?

የልጆቹ አባቶች እኮ የሚታወቁት ጥቂት ከፍ ብለው ሠፈሩ ውስጥ ከመቻል ቡችሎች ጋር እየተሯሯጡ በአፈር መጫወት ሲጀምሩ ነው። ለአንደንዶቹ እንዲያውም አፈሩ መጫወቻቸው ብቻ እንዳይመስልህ… ይበሉታል። ምነው እንደዚህ አየኸኝ?… የምነግርህን ያመንክ አትመስልም። በዚህ ዕድሜዬ የምዋሽ ይመስልሃል? ይሁን… ምንም በለኝ፣ ዝምታህን ግን ወድጄዋለሁ!

ይኸውልህ የየሺ ልጅ ይሞትና… እሱን ነው አፈር ሲበላ በተደጋጋሚ ያየሁት… አሁን አድጎ ከጎረመሰ በኋላ ነው የሞተባት… መቼም የሠፈሩ ሰው አዘነላት፡፡ ታዲያ ያዘኑላት ልጃ ስለሞተ እንዳይመስልህ፣ ከዚህ ሰፈር ሰው ልጁን ያልቀበረ ማን አለ ብለህ?… ያዘኑት አንድ ቀን እህል ጠግቦ ሳታየው መሞቱን እያነሳች ስታለቅስ ሰምተዋት ነው። እኔ ደግሞ አካፋና ዶማዬን ይዤ ሥራዬን ለመጀመር ቀብድ የሚቆርጥልኝ በአይኔ እማትርልሃለሁ፡፡

https://xtremepape.rs/

እንደወትሮው ቢሆን በቅድሚያ መቃብሩን አሳምሬ ቆፍሬ… አዘጋጅቼ… ክፍያ እጠይቅ ነበር። ብዙዎቹ በሀዘናቸው እያሳበቡ ካዱኝ… አጥብቄ የጉልበቴን ዋጋ ስጠይቅ፡- “ምነው አንተ… የልጄን፣ የሚስቴን፣ የባሌን፣ የአጎቴን… ጉድጓድ እኔ የምከድ ነኝ” በማለት ያፈጡብኛል። ነገ፣ ከነገ ወዲያ ይሰጡኛል ብዬ ስጠባበቅ ፊት ነስተውኝ ማለፍ አመጡ። ይባስ ብለው እዳቸውን ላለመክፈል እኔን… የሙታኖቻቸውን መቃብር ቆፍሬ በላቤ የማድረውን ደሀ… እንደሞት መልአክ በሰፈሩ ሁሉ እንድጠላ አስወሩብኝ። አሁን ሰፈሩ ስለእኔ ማውራት አቁሟል። ለምን መሰለህ? ሞት ጉብኝቱን ያላደረገበት ቤት የለማ! እሱ ሲመጣ እኔን ያስታውሳሉ፤ በሉ! ጓደኛውን በትረን ጥሩት ይባላላ!

ኃይለጊዮርጊስ ማሞ፣ *የተጣለው መልአክ*፣ (2006)።



https://xtremepape.rs/

**2.**

መቼም ጆሮ ጉድ ሳይሰማ አይጠባም አሉ መስከረም
እውነት ትሰቀል ተባለ? ትንጠልጠል፣ ትሙት፣ ትፈፀም?
ስጋዋ ነፍሮ ይቀቀል?
አጥንቷ ይንደድ? ይቃጠል?
ነፍሷ ይንጨርጨር? ይንበልበል?
እኮ እውነት ድራሽዋ ይጥፋ?
ዐለም ለእናንተ እንዲሰፋ
ይገርማል! መቼም ይደንቃል!
ጅብም ከማያውቁት አገር "ቁርበት አንጥፉልኝ" ይላል
"እውነት ትሰቀል!" አለ - አሉ ይህ ሀሳዊ፡ ብላ - ተኛ
እሷን መቃብር ሸኝቶ እሱ ከሞቀው ሊተኛ
እውነት ሸጦ - ለውጦስ አርፎ ይተኛ መስሎታል
እንደ ከሀዲው ይሁዳ በገዛው መሬት ይሞታል!!
አጀብ ነውእንጂ ዘንድሮ
አያግበሰብሰው ነገር "ምን አይሰማው አለ ጆሮ?"
ትላንትና ሶቅራጥስን መርዝ ቀምመው ያጠጡ
እውነተኛውን መምህር በሰላሳ ብር የሸጡ
ዘረ ያዕቆብን መቆሚያ፣ መቀመጫ እንኳ ያሳጡ
"እውነትህን ዋጥ!" እያሉ ጋሊሊዮን ያዋረዱ
ስንት እውነትን የቀበሩ - ስንት እውነትን ያሳደዱ
ዓለም በሞቀው ጉያዋ በክንዷ ያቀፈቻቸው
ከድንጋይ መውገር በስተቀር ሌላ ሙያ የሌላቸው
ዛሬ ነቃን - በቃን ስንል
የእነበለው፣ የእነስቀል፣ የእነግረፍ እህት ወንድም
ይኸው አሁን እንኳ ዛሬም
ለካስ ስጋቸው ነውእንጂ መንፈሳቸውስ አልሞተም!!
ኧረ ጉድ! አጀብ ነው! በሉ
"እውነት ትሰቀል!" አለ - አሉ?
ቀድሞስ የእርግማን ዘር - ውላጅ የክፋት፣የክርፋት ልጅ
መች ብርሀን ይበጀዋል ድቅድቅ ጨለማ ነውእንጂ!
ምሱ ምንድን ነው? ፍቱለት!
በአመድ፣ በአተላው ይውጣለት!
"እውነት ትሰቀል!" አለ - አሉ ይህ ሀሳዊ፣ ብላ - ተኛ
ግራ በቀል ልክፍተኛ
እኮ ስለምን ትሁቷ-እውነት ቅድስቷ ትቀበር?
ጠላቷ ይንጠልጠል እንጂ ባበጀው መስቀል ይቸንከር!
በቆፈረው ጉድጓድ ይግባ - ባነሳው ድንጋይ ይወገር!
ሀቅ ስለምን ትቀበር?
እውነት ስለምን ትቸንከር?

https://xtremepape.rs/

ለምን ትወገር? ትመዝበር?
“እውነት ትምከን! ዘሯ ይጥፋ! ትሙት!” አለ ይኸው ደፍሮ
“ባልበላውም ጭሬ ልድፋው” እንዳለችውእርኩስ ዶሮ
ይሁና! መቼስ ይሁና!
ግዜ ያመጣውን ገሰስ ግዜ ይወስደዋልና
የእውነት ፀሀይ ስትዳምን ሰማይ እንደ ደም ስትቀላ
የቀበሮ ባህታዊ በበጎቹ ጆርባ ታዝላ
ይበላ! መቼስ ይበላ!
ጨለማ ግዜም ተሰጥቷል ለጅብና ወሮበላ!!

ሰለሞን ሞገስ፣ *አፀሃይ በታች፣* (2004)።

https://xtremepape.rs/